




በኮሎምቢያ ዲስትሪክት

# በአደራ ቤተሰብ እንክብካቤ ስር የሚኖሩ ህፃናት እና ታዳጊዎች የመብቶቻቸው ዝርዝር መግለጫ





WE ARE WASHINGTON DC

CHILD & FAMILY SERVICES



ይህ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ በአደራ ቤተሰብ እንክብካቤ ስር በሚኖሩበት ወቅት ያሎትን መብቶች የተመለከተ ማብራሪያ ነው። የኮሎምቢያ ዲስትሪክት እነዚህ መብቶች እንዳሎት የሚገልፁ ህጎች አሉት። በእነዚህ ህጎች መሠረት የዲሲ የህፃናትና የቤተሰብ አገልግሎቶች ኤጀንሲ (CFSA) የእነዚህን መብቶች ዝርዝር ቅጂ ማግኘቶን ማረጋገጥ አለበት።ይህ ቅጂ ከጠፋቦት እና ሌላ ካስፈለጎት የማህበረሰብ ሰራተኛዎትን ወይም ሞግዚቶትን ይህንኑ ቅጂ እንዲሰጥዎት ጠይቁ። የመብቶትን  ቅፅ ወይም እና ትክክለኛዎቹን ህጎችን በኦንላይን ለመመልከት CFSA.DC.GOV ላይ በመሄድ፣ በዋናው ገፅ ላይ ከላይ ፎር ዩዝ (for youth) የሚለውን መለያ በመጫን ማግኘት ይቻላል።

## እንክብካቤዬ ምን ይመስላል

ተገቢ እንክብካቤና አክብሮት የማግኘት መብት አለዎት። ማንም ሰው ሊያስፈራዎት ፣ ሊሰድብዎት ወይም ጥቃት ለያደርስብዎ አይችልም። ማንም በመምታት ወይም በሌላ የጥቃት መንገድ ሊቀጣዎት አይቻለውም። ማንም ሰው በዘርዎት ፣ በቆዳ ቀለምዎት ፣በሀይማኖቶት ፣በተክለሰውነቶ፣ በፆታዎ ሁኔታ ወይም በእክሎ ምክንያት እርዳታን ከማቅረብ ሊቆጠቡቦት ወይም ክብር ሊያሳጣዎ አይችልም። አዋቂ ሰዎች ጥሩ እንክብካቤ ያቀርቡሎታል። ሊጠብቆት እንዲሁም በመልካም መንገድ እንያስቡ እና እንዲንቀሳቀሱ ሊረዱዎት ይገባቸዋል። ማድረግ የሚፈልጉትን ነገሮች እንዲያደርጉ ያግዞታል። በሚገባዎት ቋንቋ ያናግሮታል። የሚኖሩበትን ቦታ ፣ ሰዎች እያስተናገድዎት ያሉበትን ወይም እያገኙ ያለውን እርዳታ የተመለከተ ማንኛውም የሚያበሳጮት ነገር በሚኖርበት ወቅት የመናገር መብት አሎት። የሚያሳስቦትን ነገር ሲያቀርቡ የቡድን አካላት እና ኤጀንሲዎ ሊያደምጥ ይገባል። በተቻለ ፍጥነት ችግሮትን መቅረፍ ይጠበቅባቸዋል። በመናገሮ ምክንያትንም ማንም ሊቀጣዎት አይችልም።

# በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአደራ ቤተሰብ እንክብካቤ ስር ያሉ ህፃናት እና ታዳጊዎች መብቶች ዝርዝር መግለጫ

## በልጅ እንክብካቤ አገልግሎቶች ወይም ውሳኔዎች ላይ ደስተኛ ካልሆኑ ምን ማድረግ ይቻላል?

### በመጀመሪያ የአገልግሎት አቅራቢ ቡድኖትን ማነጋገር

▶ በመጀመሪያ የማህበረሰብ ሰራተኛዎትን ማነጋገር። ችግሮትን በግልፅ ያቅርቡ።

▶ በተመመሳሳይ የስልጣን ተዋረድ ያሉ ሌሎች አካላትን ሱፐርቫይዘር ወይም የማህበረሰብ ሰራተኛን ማነጋገር። (የሲኤፍኤስ) የማህበረሰብ ሰራተኛ ጋር ሲደውሉ የድምፅ መልዕክት ማስቀመጫን በመጠቀም ከመልዕክት ማስቀመጫው የሱፐርቫይዘሩን ስምና ስልክ ማግኘት ይችላሉ)።

▶ በበድኖት ውስጥ ያሉ አሳዳጊ/ ሞግዚቶችን ማነጋገር። ችግሮትንን በግልፅ ማቅርብ። እርዳታንም መጠየቅ።

### "YO BUD" ን ማነጋገር

▶ እድሜዎ ቢያንስ 14 ከሆነ ከላይ የተጠቀሱትን ሂደቶች ሞክረው ካልተሳካ የሲኤፍኤስኤ የታዳጊዎች ዕንባ ጠባቂ ክፍል (በሌላ ስሙ "YO Bud" ) ሊረዳዎት ይችላል። የመኖሪያ ሁኔታ ማስተካከያዎች፣ መብቶች፣ እና ተገቢ አያያዞች YO Bud ከሚከታተላቸው ጉዳዮች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው።

▶ YO Bud ን ለማግኘት 1-855-874-3273 መደወል ወይም በኢሜይል አድራሻው yo.bud@dc.g መጠቀም ይቻላል።

## ቡድኔ

የአግልግሎት ቡድኖት በእርሶ ጉዳይ ላይ የሚሰሩትን ሰዎች ሁሉ ያካትታል። በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ በአደራ እንክብካቤ ስር ሳሉ ያሎትን የማህበረሰብ ሰራተኞትን አሣዳጊዎትን እና ሌሎች በቡድኖት ውስጥ ያሉትን ሁሉ የማወቅ መብት አሎት። የማህበረሰብ ሰራተኛዎ በየጊዜው ይጎበኞታል። የማህበረሰብ ሰራተኛዎ በተገቢው ወቅት የስልክ መልዕክቶትን እንደሚመልስልዎ መተማመን ይችላሉ። ፍርድ ቤት ጉዳዮትን ለማዳመጥ ሲቀመጥ ሱፐርይቫይዘርዎ ያሳውቆታል። ከፈለጉም የችሎትን ሂደት መከታተል ላይ ይዘዎት ሊሄዱ ይችላሉ።

## የግል መረጃዬን እና ምስጢሬን በተመለከተ

ለምን በአደራ እንክብካቤ ስር እንደሆኑ የማወቅ መብት አለዎት። በእርስዎ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ ሰዎችን (ቡድኖትን) የማወቅ መብት አሎት። ለእርስዎ የሚያደርጉትን ውሳኔዎች ሁሉ ሊያሳውቆት ይገባቸዋል። በቂ እድሜ ላይ ሲሆኑ እራዎ ምርጫዎችን እንዲያደርጉ ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ ያደርጎታል። እርስዎን የተመለከቱ መረጃዎች ምስጢራዊ ናቸው። በእርስዎ ቡድን ያሉ ሰዎች መረጃዎትን ለውጭ ሰዎች አያካፍሉም። የሚኖሩበትን ቦታ ህጎች እስከጠበቁ ድረስ የግል ንብረቶችዎን በግሎ መጠበቅ ይችላሉ። ስልክ የመደወል ተግባር ወይም ኮምፒተርዎትን በግል ቦታ በሚስጥር ማድረግ ይችላሉ።

በ18 አመት ዕድሜ ላይ ደርሰው የማደጎ ቤቶትን ከመልቀቅዎ ከ30 ቀናት በፊት ወሳኝ የግል ሰነዶችዎን

- የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር
- የመታወቂያ ወረቀት
- የልደት የምስክር ወረቅት
- የኢሚግሬሽን ሰነዶች(ካሉ)
- የጤና ሪፖርቶች እና የህክምና ኢንሹራንስ እንዲሁም
- የትምህርት ማስረጃዎትን ይበላሉ።

ከ18 አመት በፊት ከለቀቁ የማህበረሰብ ሰራተኛዎት እነዚህን ሰነዶች ለቅርብ አሳዳጊህ ወይም ለህጋዊ አሳዳጊ ይሰጣል።

## በእንክብካቤ ስር እያለሁ የምኖርበት ቦታን በተመለከተ

በአስተማማኝ እና ንፁህ ቦታ የመኖር መብት አሎት። ልዩ ሁኔታ ከሌለብዎ በቀር በተመሳሳይ ትምህርት ቤት የመቀጠል መብት አሎት። ቡድንዎ እንደ፡-

- ትምህርት ቤት
- ከትምህርት ቤት ቀጥሎ ያሉ ተግባሮች
- ዶክተሮችህን የማየት
- ስራዎት
- ቤተሰብ የማየት እና
- ሌሎች የሚፈልጉትን ጉዳዮችን ለመካፈል ለመሄድና ሄዶም ለመመለስ መቻል ላይ ምቹ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት።

የፈጉትን ሀይማኖት አስተሳሰብ የመከተል መብት አሎት። ከሀይማኖትዎ ውጭ ወደሆኑ ሀይማኖታዊ ስርአቶች ያለመሔድ መብት አሎት። የአሳዳጊ ቤተሰብዎ ምቾት እንዲሰማዎት ሊረዳዎት ይገባል። ይህን ለማድረግ አንዱ መንገድ በቤተሰባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማሳተፍ ነው።

## ቤተሰቤ

ከቤተሰብህ ወይም ለእርስዎ ጠቃሚ ከሆኑ ሌሎች ሰዎች ጋር ግኑኝነትዎን የመጠበቅ መብተ አሎት። ከነሱም ጋር መደበኛ ጉብኝት የማድረግ እና በስልክ ወይም በኢሜይል መገናኘት ይችላሉ። የቡድን መኖርያ ቤት የሚኖሩ ከሆነ ቤተሰብህዎ የቡድን መኖሪያ ሰራተኞችን የማነጋገር ፈቃድ ማግኘት ይችላል። ጥያቄዎች ካሏቸውም በፍጥነት መልስ ማግኘት አለባቸው። የአገልግሎት ቡድንዎ የተወሰኑ ግኑኝነቶች አደጋ እንዳላቸው ካላሰቡ በቀር እነዚህ መብቶች አላቸው። ይህ ካልሆነ ግን የእርስዎ ደህንነት ስለሚቀድም የተወሰኑ ገደቦችን ማኖር ይጠበቅቦታል።

# በኮሎምቢያ ዲስትሪክት በአደራ ቤተሰብ እንክብካቤ ስር የሚኖሩ ህፃናት እና ታዳጊዎች መብቶች ዝርዝር መግለጫ



## ጤናዬን በተመለከተ

ጥሩ እና መደበኛ ህክምናን ከዶክተር፣ ከጥርስ ሀኪምና ከዐይን ዶክተር የማግኘት መብት አሎት። አልኮል ወይም መድሀኒት የመጠቀም ሁኔታ ካስፈለጎ የሚመለከተው የባለሙያዎች ቡድን የምክር አገልግሎት ማግኘቶትን ማረጋገጥ ይኖርበታል። በጤናማነት ለመቆየት ምን ማድረግ እንዳለብዎት ዶክተሮን ማነጋገር አለቦት። ስለጤናዎ ሁኔታ እንዲያብራራልዎ  የሚከታተልዎትን ዶክተር መጠየቅ ይችላሉ - ስለሚፈልጉት ነገር ማነጋገር ይችላሉ ። ጤናማ አመጋገብ የማግኘት መብት አሎት። በሀይማኖት፣ በጤና ወይም በሌሎች ምክንያቶች የሚመገቡትን ምግቦች ካሉ አዋቂዎች የሚመገቡትን ሊያዘጋጁልዎ ይገባል።አዋቂዎች ንፅህና እና ጤንነትዎን ለመጠበቅ እንዲችሉ የራስዎትን ሳሙና ፣የጥርስ ቡሩሽ እና ሌሎች የግል ንፅህናን የመጠበቂያ መሳሪያዎች ሊያቀርቡልዎ ይገባል።

## የግል ንብረቶቼን እና ገንዘቤን በተመለከተ

ልብሶትን እና የግሎት የሆኑ ንብረቶችን ወደ ማደጎ/የአደራ ቤት ይዘው መምጣት ይቻላል። በሚዘዋወሩበት ወይም ማደጎውን ሲለቁ ንብርትዎን በሙሉ መውሰድ ይችላሉ። በማደጎው ጊዜ አሳዳጊዎች ለእያንዳንዱ ወቅት የሚሆኑ በቂ ልብሶችና ጫማዎች እንዳሎት ማረጋገጥ አለባቸው። እነዚህም ለትምህርት ቤት ዩኒፎርም ወይም ከፈለጉም ለስራ የሚሆኑትን ያካትታል። የሚለብሱትን ልብሶች በተመለከቱ አንዳንድ የመምረጥ መብት አሎት። የገንዘብ አያያዝን ማወቅ ይጠቅማል። የገንዘብ ቁጠባ ሂሳብ መክፈት ላይ እና እንዴት መጠቀም እንደሚገባ ለማወቅ የባለሙያ ቡድኑ ይረዳዎታል። እድሜዎ 14 አመት ሲደርስ ቡድኖ የግል ሂሳቦን ሁኔታ በየአመቱ እንዲያረጋግጡ ይግዞታል። የግል ሂሳብ ስርቆት አደጋ ስለሚኖር የክሬዲት ሪፖርቱን ልክ መሆኑን ማጣራት አለቦት። ያገኙትን ማንኛውም ችግሮች ለማስተካከል ቡድኖ ያግዞታል።



## ለወደፊት ሁኔታዬ የሚያስፈልጉ ነገሮች

ለዕድገት አስፈላጊ ከሆኑ ዋናው አካል ለወጣትነት ህይወት እየተዘጋጁ ማደግ ነው። መሰረታዊ ትምህርት ከአፀድ ህፃናት እስከ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቅ ያስፈልጎታል። ቡድኖ ትምህርት ቤት ሙመዝገብዎትን ማረጋገጥ አለበት። ትምህርት ቤት ለመሄድ ፣ ለመማር ፣ ለመመረቅ የሚያስፈልጎትን ነገሮች እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው። በስፖርት በክለብ እና በሌሎች የትምህርት ቤት ውስጥ እንቅስቃሴዎች ተሳትፎ ላይም እገዛ ያደርጉሎታል። የማህበረሰብ ሰራተኛዎ የመንጃ ፈቃድ ወይም የግዛት የመታወቂያ ወረቀት እንዲያገኙ ሊያግዝዎ ይገባል። እድሜዎ በእንክብካቤ ስር ለመኖር የሚፈቀድበትን ደረጃ ካለፈ ቡድኖ የሽግግር ወቅት ዕቅድን እንዲፅፉ አብሮት ይሰራል። በዕቅዱ ውስጥም ከማደጎ እንክብካቤው ቀጥሎ እንዴት እራስዎን  እንደሚያስተዳድሩ በስዕላዊ መግለጫ ማብራራት አለብዎ። ለምሳሌ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሃላ ምን ለማድረግ እንዳሰቡ -ኮሌጅ ልዩ ስልጠና ወይም ስራን መምረጥ አለቦት።

# በኮሎምቢያ ዲስትሪክት በአደራ ቤተሰብ እንክብካቤ ስር የሚኖሩ ህፃናት እና ታዳጊዎች መብቶች ዝርዝር መግለጫ

## የሕግ ማጣቀሻወች

ይህ የመብቶች ዝርዝር መግለጫ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአስተዳደር ደንብ መመሪያዎች ርዕስ 29 የህዝብ አስተዳደር ፦

- ምዕራፍ 60 የአደራ ማሳደጊያ ቤቶች ክፍል 6004.1
- ምዕራፍ 62 የታዳጊዎችን መጠለያዎች፣ የድንገተኛ እንክብካቤ ተቋማት እና የታዳጊዎች ቡድን መኖሪያ ቤቶች ፈቃድ አሰጣጥ ክፍል 6203
- ምዕራፍ 63 በግል የመኖር መርሃ ግብሮች ክፍል 6303.1



CHILD & FAMILY SERVICES




**DC Child and Family Services Agency**
**200 I St SE, Washington, DC 20003**

**cfsa.dc.gov | dc.mandatedreporter.org**
**fosterdckids.org | adoptdckids.org**

**202.442.6100**

**/CFSADC**

**@DCCFSA**